የተክልየ ማስታወሻ .... ሽሙጥ

ከሰሜናዊት ከተማ

እነሆ ወደ ዱሮ ቤቴ ከተመለስኩ ይሄው አስር ወራትን አስቆጠርኩ፤ ሌሊቱን በሙሉ መባነኔ አሁንም አልለቀቀኝም፡ ... አዲስ አበባ ያለሁ እየመሰለኝ በህልሜ የግቢዉ በር በሃይል ሲደበደብና ስበረገድ እየሰማሁና እያየሁ ባንኜ ከእንቅልፌ እነቃለሁ። የኛው ሰዎች ሲያደርጉት እንደነበረው ዛሬም በምሽት የሰው በር እይበረገዱ መያዝ ያለ የሌለ መሆኑን ባለማወቄ...     በየቀኑ የህልም ጭንቀት ያስቃየኛል ... ታዲያ አንተው ውድ ወዳጄ ወዳዘጋጀህልኝ ቤቴ መመለሴን ምነው በእንቅልፌ ረሳሁት ... ዛሬ ተክልዬን በሩቅ ሳይሆን እደጃፍ ደርሼ መሳለም ማን ከልክሎኝ... የሀገር አዲባር ከደጄ ነው። እኔ እንኳ ደህና ነኝ ... ዋ! አንተን ውድ ወዳጄን ወደዛው ልኬ ለአደጋ መዳረጌ ያሳስበኛል። ብቻ አንተ አዋቂ ነህና ከአደጋ ራስህን መሰወር አይሳንህም፡ .. ሁሉንም መንገድ እያስያዝክ ስለመሆኑ እናም በጤና እንዳለህ ከአንተ ባልሰማም የድርጊትህን ውጤቶች በየቀኑ በተለያዩ ዜና ማሰራጫዎች እስማለሁ።

ውድ ወዳጄ፤ ልክ እንደገመትነው ሁሉም ተጠቃሎ ወደ ሀገር ገብቶአል። አሁን ለትርምሱ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮልናል። ወደ አለፈው ከፍታ ... ከፍታ ይህችን የወዲ ስምኦን ቃል አልውዳትም ... የሚያመወን ጎዳና.. በረጂሙ እንደሆን እንጂ በአጭር ጊዜ እንደማይቻል ባለፈው ግምገማ ላይ አስምረንበታል። ዛሬ አላማችን ያው ቢያቅተን “ትናንት ከዛሬ ይሻላል” ህዝቡን ለማስኜትና ደጉን የሰላም ዘመን ህዝቡ እንዲናፍቅ ማድረግ ነው። ይህ ከሆነ የኛ አላማ ሰክኖአል ማለት ነው።  ያ ካልሆነ የኛ ነገር አበቃም አይደል?

ያው ከዝህ ስትነሳ የነገርንህን ... ጣምራ ግባችንን ሁሌም አስታውሳቸው ..የሚኒልክን ቤቴ መንግስት የተቆጣጠሩትን ወገኖች ጀርባ ማተራመስ .... የሚኒልክን ቤቴ መንግስት በእጁ መልሶ ለማስገባት ከዛሬዎቹ የቤቴ መንግስት ተቆጣጣሪዎች ጋር የስልት ትብብር የፈጠረውን የተዳፈነ እሳት ከጭዱ ጋር እንዲጋጋል ማድረግ .. ረስተሃቸዋል ብየ አይደለም ... እንዲያው ራሴም ላስታውሳቸው ብየ እንጂ .. ዋ ይሄ ከተሳካ ስለ እኛ ማውራት ይቆማል .. ዛሬ ያለንን ይዘን መዝለቅም ይቻለናል ... ከበረታን ... ይህ ከሰመረ የኛ ዘመን ናፍቆት በአዲስ ሲዘፈን ታየኝ። ይሄን ለማሳካት ተክልዬ ካንተ ጋር ይሁን ብለን መርቀን ልከንህ የለ ....

እንደታዘብኩት ለማ ኦሮሚያን መቆጣጠር እንዲሳነው ያው የሁለት ጎንዮሽ ውጋት ገጥሞታል። “ኢሱ” ያሰማራው ዳውድ በአንድ ጎን .. ራሱን እንደመንግስት የሚቆጥረው፤ በየቀኑ አክሮባት የሚሰራው፤ ያ የአሜርካው ልጅ ..የእግር እሳት ሆነውበታል። ፋታ ነስተውታል። ያን ሰሞን ሰግተን የነበረው ኢሱ ዳውድን ለአብይ ታዘዝ ብሎ ልኮት ይሆን ብለን ነበር። የተክልዬ ፈቃድ ሆኖ ስጋታችን በነነ። ያልተረዳነው የኢሱ የስለላ መረብም አብይን ማዳከም እንደሚፈልግ ነው... አሁን ግልጽ የሆነው የኢሱ ሰዎች ዳውድን ተጠቅም አብይን አዳክሞ ... አብይን በውለታ ጠያቂነት የኢሱ ጥገኛ ለማድረግ የወጣ ስልት ያለ ይመስላል። አለያማ ማን ይሙት በኢሱ ቤት ሰልጥነው በኢሱ ትዛዝ የሚንቀሳቀሱተ እነ ዳውዲ እንዲያው ተነስተው አብይን ይፈታተኑ ነበርን ? እኛስ እንዴት እድለኞች ነን... በኢሱ በተከፈተው መንገድ ... መቼም ገንዘብ፤ የወታደር ልብስ፤ መሳሪያ የማይቀበልህ የለምና ደረስንላቸው። ዋ ገረገራው የኦሮሞ ህዝብ ትናንት ያልነበረ ታጣቂ .. ስንቅና ትጥቅ ከየት መጣ ብሎ አይጠይቅ.... አንተም እንዳልከው የሚታዘዝ ሳይሆን ራሱን የሚያዝ ታጣቂ ማበራከቱን ስራችን ብለን ከተያያዝን የሰደድ እሳት በኦሮሚያ እናቀጣጥላለን። ... ዛሬ እንደሰማሁት ያ ውጪ ሀገር ያለ ወዳጄ ውጭ ያለውን የኦሮሞ ማህበረሰብ በተለይም ከወለጋ የመጡትን አስተባብሮ በአብይና በለማ ላይ በታላቅዋ የአለም መዲና ሳይቀር የተቃውሞ ሰልፍ እንዲወጡ እየስራ ነው ... ለዚህ ደግሞ ያው ጀዋርና አጋሮቹም በየቀኑ በሚቀያየረው አቋማቸው ቀውሱ እንዲባባስ እየረዱን ነውና ባንካቸው እንዳይነጥፍ ለወዳጆች ማስታወሱን አትዘንጋ።

ይሄው ሰሞኑን በወለጋ የተጀመረውን ወደ ባሌ ወደ ቦረና ወደ ምስራቅ ሀረርጌ ማሻገር ተጀምሮአል። ..ሬንጀር ለባሽ ወጣት ሲያይ ልብ የማይሸፍት ኦሮሞ እስካሁን እንዳልገጣመህ ከመልክትህ ተረዳሁ... ያው ብዙ ዘመን በቄኤአቸው ልያዩት የተመኙትም አይደል ... ጊዜው ካለፈ መሆኑን ማን ባስታወሳቸው.. ዎ ክላ... መካሪያቸው ማን

አደረገኝ.. ያው እኛም የገድሉን ተዋንያን ማስተዋወቁን ከዚህ ተያይዘናል .... መሮ መሮ እያልክ ማዘመሩን አንተም ግፋበት... ዋ ወዲ አሰፋ ጥሎ አልጣለንም ... ለአንድ ቀን ያላቸው ልጆቹ ስራቸውን በሁሉም ክልል ተያይዘውታል ... ግን አንተም እንዳልከው የማሸነፋችን መሰረቱ ኦሮሚያ ነው..

አንዳንዴ የመሀሉን ዜና ስሰማ ያስፈራኛል፤ ያን ሰሞን የሌንጮው ኦዴድ ከለማ ጋር አንድ ሆነ ሲሉኝ ደነገጥኩ .. ታዲያ የለማ ልጆች ከአርቆ አሳቢነን ከስልት ድህነት ለመላቀቅ መወሰናቸው ታየኝ ። ግና ያው በኛ ዘመን ያደጉም አይደል ..ሳያውቁና ያለጥበብ በራስ እንዲኩራሩ ስላደረግናቸው ... ምክር መጠየቅና መውሰድ ..በጉዳዮቹ ላይ ማማከር ያልለመዱት ስለሆነ ... ካልተቀየሩ የትም አይደርሱም አልኩ ..እንዲሁም እነ ሌንጮም ጥንት እንደማውቃቸው ሳይጠየቁ መምከር ..ሳይጠሩ መሄድ እንደ ሀፍረት ስለሚቆጥሩ ያንን ቁመናቸውን ካልቀየሩ ትብብራቸው የቅርበት ሰለማይሆን አያስፈራም እያልኩ ስጽናና ሌላ ጉድ መንገድ ላይ እንዳለ ሰማሁ። ያ የተማሪነት ዘመን ባልንጀራዬ ... ተሟጋቹ ዮሃንስ (ክላ ... ገላሳም አይደል የዛሬ ስሙ.. ) ወደ ሀገር መመለሱ ነው አሉኝ..... ሌላ ቅመም ለመጨመር ... በእርሱ በኩል የሚያሰጋኝ ... ወይ እንደ ሌንጮ ከነለማ ከወገነ ... የእኛ ጉዳይ አበቃለት ..ያ የቁቤ ... ምን ነበር የሚሉት.. ብርሀነ ቁቤ .. ሰውየም ከእርሱ ጋር ይመጣል አሉ። ይሄኛው ዩሐንስ እንደ ታላቅ ሞክሼው አይደለም ... ትዝ ይለሃል ወዲ ዜናዊን ስያሰጨንቀው ... ሃሳቡን ከመስንዘር ፤ መንገድ ከማሳየትና ከማስያዝ .. ወደ ኃላ የሚል አይደለም ... ደግሞም እንደ ዳውድ ሌላ ጌታ የለው .. የህዝቡ አሽከር ነኝ ነው የሚለው አሉ። ... ብቻ ያችን የኦሮሚያን ሪፓብልክ እንመሰርታለን የሚለውን .. አሁን የኢትዮጵያን መንግስት ተቆጣጥረናልና ጊዜው አልፎበታል ካለና ከነለማ ካበረ ... ወይ ጉድ ልያስኝ ይችላል... ኦነግም ቢሆን በአንድነት በነበረበት ዘመን የሚያውቀው መሪም እርሱ አይደለምን.. ዳግም ሁሉን ኦነግ ባንድ ላሰባስብ ካለ ይሳነዋልን? የገላሳን ጉዳይ በቅርብ ተከታተሉ፤ ጊዜ እየጠበቃችሁ በእርሱና በለማ መሃል ሽብልቅ ክተቱ... ያን እንቅልፋም ደግሞ ጊዜው አሁን ነው በለው..መተኙቱን ያቁም፤ የዚህ ሰው እርምጃ ...የኛንም ህልም ልያመክንብን ይችላል ... ተክልየ ከዚህ ይሰውረን ።

ገዱን መገፋፋቱን ሰዎቻችን ቀጥለውበታል ... ቀስ በቀስ ከኦሮሞዎች ጋር ግጭት እንዲፈጠር መገፋፋት ጀምረዋል.. አዲስ አበባ የመጨረሻው እሳት መለኮሻው ትሆን ዘንድ አሁን የአዲስ አበባ ጉዳይ አታንሱ፤ ምንም እርምጃ እንዳይወሰድ መረብ ጣሉ .. መንግስትም ለቄሮ ጥያቄዎች ምንም መልስ እንዳይሰጥ እየሰራችሁ ይለውን አሁንም ቀጥሉበት .... ዛሬ ለጥያቄዎቻቸው መልስ ከተሰጠ.. እሳተ ጎመራው ሳይግል ሳይታመቅ ፈነዳ ማለት ስለሆነ እነ አብይ ልቆጣጠሩት እናም የሚያስከትለው ጉዳትም ትንሽ ልሆን ይችላል ... ስለዚህም ነው .. የአማራው ብሄረተኛ እስከጠናከር፤ አዲሴዎች ራሳችውን እስኪያሰባስቡ፤ አዲስ አበባ ጉዳይ እንዲዘገይ ማበረታታት ቀጥሉበት.. እንደተነጋገርነው እንዳይጠፋ ነካኩት .. ግን እዛው ታፍኖ ይጋጋል .. የመጨረሻውን ፍንዳታ ቀን ይጠብቅልን። ያ ልክፍተኛ የጥንት ወዳጃችን የዱላ አባት ያንን የደርግ ዘመን ሀያ አምስት ከፍተኛ የአዲስ አበባ ድንበር እያለ ያወራል አሉ... እንዳይጮህ አትነካኩት ... እንደ ፌዴራል ቋንቋ ሁሉ ይሄም አድሮ ይጋል ... ለመጨረሻው ትርምስ... ይሰንብት። ... ኦ አንዳንዴ እኛው የቀረጽናቸው ሰዎች መሆናቸው በጆቶናል .. መወሰን ይሳናቸዋል .. ተራራው እያደገ ሲሄድ እያዩ .. ሌላ ሰው እንዲወስን ስጠብቁ ሳይ ምን አይነት ሰው እንደፈጠርን ይገርመኛል።

ውድ ወዳጄ .. አንተ እየሰራሄው ያለውን እነርሱ በራሳቸው ላይ እንደ ማሞ ቂሎ እየሰሩ ካለው ስራ መለየት አቅቶኝል ። ሩቅ ስለሆንኩ መሰለኝ ... የለግላጋዋ ቤት ጫወታም ሙሉውን መስማት ካቆምኩ ሰነበተ... ብቻ ማሞዎችና አዲሶቹ ደንበኞች ማዘውተር መጀመራቸውን ያ ወዳጃችን ከላከው ማስታወሻ ተረዳሁ... ዘመንም እንዲህ በአጭሩ ይለዋወጣል ... ምነው የእርሷ ኩራትዋ... ያሳለፈችውን እንዲህ ባጭር መርሳትዋ... ከማስታወሻው እንደተረዳሁት .. የእርስዋ ምልምሎች ... አዲሶቹን ከተሜዎች እያስተናገዱ ነው፡ መረጃ ያው በሽበሽ ነው። ያንን ከአሜርካ የመጣውን ሰው በደንብ እንድትይዘው አድርግ .. አንተም አትፍራት ተጠጋት። ምንም ቢሆን የኛው አይደለች.. ህይወትዋን የገነባን እኛው አይደለን ... አትራቃት አታስቀይማት .... ክላ .. አሁንስ ቅናት ቢጤ ነገር ያዘኝ ... ምን እያልኩ ነው ..... የትንሽ ከተማ ነዋሪ ሆኜ ተቸገርኩ.... አንዳንዴ የትናንት ህይወትን ማስታወስ ያበሳጫል .. በቃ ተክልዬ ይታረቀኝ፤... በሰላም ክረምልኝ .. ተክልዬ ይጠብቅህ... ደህና ሰንብት።